ግንቦት 6 ቀን 2005 ዓ.ም.(May 14/13)

# የሸንቁጥ ልጆች *

( በዛሬው ቀን ይህ የአርበኞች የፎቶግራፍ ስዕል ለአዲስ አበባ ዩኒቬርሲቲ የተበረከተበትን ምክንያት በማድረግ ከፋሽስት ኢጣሊያን ወራሪ ሀይል ጋር ለአምስት ዓመታት ፍልሚያ ያካሄዱ ጀግኖች ወንድማማቾች ታሪክ አጭር መግለጫ)

የፋሽስት ኢጣሊያን ጦር ኢትዮጵያን ወሮ መናገሻ ከተማዋን አዲስ አበባን ለመያዝ ሲገሰግስ አልጋው ፈርሶ ንጉሠ ነገሥቱም ወደ ስደት ሲያመሩ ቆራጥ የኢትዮጵያ ልጆች "ዱሩ ቤቴ" በማለት የጎበዝ አለቃቸውን በመምረጥ የጠላትን ሀይል ለመመከትና ከአገር ለማባረር ሁሉም ሲንቀሳቀስ ከአምስቱ የቀኛዝማች ሸንቁጥ ደራጅ ልጆች ውስጥ ሦስቱ፤

1. ሻለቃ ተሾመ ሸንቁጥና
2. ልጅ ሀይሌ ሸንቁጥ የአጼ ኃይለ ሥላሴ ቤተ መንግስት ጠባቂዎች፤
3. ልጅ አበበ ሸንቁጥ በፖስታ ሚኒስቴር የኮድ ክፍል ሀላፊ የነበሩ

ተያይዘው አባታቸው ወደሚኖሩበት ወደ መርሀቤቴ ለመሄድ ወሰኑ፡፡ ቤተሰቦቻቸውንና ጉዛቸውን ይዘው ወደ ኮራ መርሃቤቴ ሚያዝያ 28 ቀን 1928 ዓ.ም. በመሄድ ከአባታቸው ከቀኛዝማች ሸንቁጥ ደራጅና ከባለቤታቸው ወይዘሮ ማሚትና አባታቸውን እየረዱ በእርሻ ከሚስተዳደሩት ሁለቱ ወጣቶች ወንድሞቻቸው፤

1. ከልጅ ይነሱ ሸንቁጥና
2. ከልጅ ጥላሁን ሸንቁጥ ጋር በሰላም ደርሰው በመገናኘታቸው ሁሉም በደስታ ተዋጡ፡፡

አገር ተወራ ሠላም አለመኖሩን ተገንዝበው የሁሉም የሸንቁጥ ልጆች ታላቅ ወንድም ግራዝማች ተሸመን መሪ በማድረግ አገሬውን የመቀስቀስ ሥራ ላይ ተሰማርተው በመዘዋወር ሙሉ ሀይላቸውን ተጠቀሙበት፡፡

ግራዝማች ተሸመ፤ ልጅ ሀይሌና ልጅ አበበ በመስከረም ወር 1929 ዓ.ም ወደ ፍቼ በማምራት ከደጃዝማች አበራ ካሣና ከሻለቃ መስፍነ ስለሺ (በኋላ ራስ) ጋር የፋሽትን ሀይል

በመረዳዳት ለመመካከር ሄደው ተወያይተው ወደ መርሃቤቴ ተመልሰዋል፡፡

በተመሳሳይ ከባላምባራስ አበበ አረጋይ ( በሁዋላ ራስ) ጋር ለመወያትና ለመረዳዳት ከአንድዬም ሁለት ጊዜ ወደ ጅሩ አፋፍ በመሄድ ተመካክረው ተመልሰዋል፡፡

ከልጅ ከፈለው ወልደ ጻዲቅ ( በሁዋላ ደጃዝማች ) ጋር ከመወያትም በላይ ከግራዝማች ተሸመ ሸንቁጥ ጦር ጋር የልጅ ከፈለው ጦር ተቀናጅቶ የጠላትን ጦር ገጥመው ዝርክርኩን አውጥተውታል፡፡

ሁሉም ወንድማማቾች አንድ ላይ በመንቀሳቀስ የጠላትን ግዙፍ ሀይል ሲመክቱ ቆይተው የተከታዮቻቸው የሰው ሀይል እየጎለበተ በመሄዱ ከ1930 ዓ.ም. ጀምሮ ግራዝማች ተሸመ፤ ልጅ ሀይሌ እና ልጅ አበበ የየራሳቸውን ጦር በማደራጀት ጠላትን በየፊናቸው ፊት ለፊት ይገጥሙት ጀመር፡፡ የጠላት ሀይል በአንዱ ላይ ሲጠነክር ይተጋገዙ ጀመር፡፡ የጠላት ጦር ከካምፑ እንዳይወጣና እንደልቡ እንዳይነቀሳቀስ ወጥረው ይዘውት ነበር፡፡ የወንድማማቾቹ ጦር ድል እየተጎናጸፈ በመሄዱ የጠላት ጦር ከመጨነቁ የተነሳ በሰላማዊው ሕዝብ ላይ በአውሮፕላን የመርዝ ጢስ እስከማርከፍከፍና የሠላማዊን ሕዝብ ሕይወት በመቅጠፍና አካለ ስንኩላን ከማድረጉም በላይ የእህል ማሳዎች እንዲመክኑ አድርጉዋል፡፡

በዚሁ የአምስት የወረራ ወቅት ከአምስቱ ወንድማማቾች የሸንቁጥ ልጆች ውሰጥ ሦስቱ በግፍ ተጨፍጭፈው ከመገደልም በላይ አካላቸው ተቆራርጡዋል፡፡

ከወንድማማቾቹ የመጀመሪያው ተጎጂ ወጣቱ ልጅ ይነሡ ሸንቁጥ ነበር፡፡ እሱም በጠላት በተሰነዘረ ጥቃት በጥይት ተመቶ እንደወደቀ የጠላት ሀይል ደርሶ ሰውነቱን በመተልተል ሰልበውትም ሜዳ ላይ ወድቆ ትልቁ ወንድማቸው ግራዝማች ተሸመ ሬሳውን አፈላልገው በማግኘት በመሪር ሀዘን ቀሪውን አካሉን እዚያው እዱር ውስጥ ቀብረውታል፡፡

በመቀጠልም ልጅ ኃይሌ ሸንቁጥ በተለያዩ ውጊያዎች ጀግንነታቸውን ያስመሰከሩ ደፋር ጎልማሳ ነበሩ፡፡ ታሞ ላይ በተደረገ እጅግ የተፋፋመ ጦርነት ላይ በግራ በኩል ልጅ አበበ ሸንቁጥ ጦራቸውን አሰማርተው ሲመክቱ በቀኝ አቅጣጫ የሚመጣውን የጠላት

ጦር ደግሞ ልጅ ሀይሌ ሸንቁጥ ጦራቸውን አደላድለው ሲመክቱ የጠላት ጦር እንደጎርፍ እየተበራከተ በመምጣቱ በመጀመሪያ ልጅ አበበን ከፉኛ አቆሰላቸው፡፡ አብረዋቸው ያሉት አርበኞች እሳቸውን በቃሬዛ ገለል እንዳደረጉ ልጅ ሀይሌ የጠላትን ሀይል እየተከላከሉ ሲያፈገፍጉ ወዲያውኑ ልጅ ሀይሌም ከፉኛ ቆሰሉ፡፡ ቆስለው እንደወደቁም ሊማርኩዋቸው የሚመጡትን የጠላት መሣሪያዎች አንድ ባንድ በመረፍረፋቸው ከሩቁ ቦምብ ወርውረው ደመሰሱዋቸው፡፡ ከዚያም አንገታቸውን ቆርጠው ጭንቅላታቸውን ለአለቆቻቸው የምስራች ወደ አዲስ አበባ ላኩት፡፡

ሦስተኛው የሸንቁጥ ልጅ ፤ ልጅ ጥላሁን ሸንቁጥ በ1933 ዓ.ም. መግቢያ ላይ አርበኛው የንጉሡ ነገሥቱን ወደ አገር መግባት በመጠባበቅ ላይ እያለ የጠላት ሀይል በሌሊት ተሸሎክልኮ አርበኞች ሰፈር በመድረስ ተኩስ ከፍቶ



**ይደመቆ በተባለ በረሃ በሰኔ ወር 1932 የተነሳ ፎቶግራፍ**

ከግራ ወደ ቀኝ መሃል ዝቅ ብለው የተቀመጡት ማሞ ሥዩም ( በሁዋላ ደጃዝማች)፤ ከፍ ያለ ወንበር ላይ የተቀመጡት ግራዝማች ተሸመ ሸንቁጥ ( በሁዋላ ደጃዝማች)፤ አጠገባቸው ወንበር ላይ የተቀመጡት ልጅ አበበ ሸንቁጥ ( በሁዋላ ደጃዝማች) ፤አጠገባቸው ልጅ ተድላ መኮንን( በሁዋላ ሜ/ጌኔራል) አሳቸው ላይ የቆመው ሕጻን ዓለማየሁ አበበ( በሁዋላ አምባሳደር)፡፡ ከግራዝማች ተሸመ ሸንቁጥ ጀርባ ወጣት ጫንያለው ተሸመ ( በሁዋላ አምባሳደር)፡፡ ፊት ለፊት መሬት ላይ ከተቀመጡት በመሃል ምልኬ ጩፋ (በሁዋላ ግራዝማች) በቀኝ ከሳቸው አጠገብ አጋፋሪ ሸሽጉ፡፡ ከጀርባ ከቆሙት መካከል ይታገሱ ጢጋው መታፈሪያ አዲሴ ካሣ የሚባሉአሉበት፡፡

ልጅ ጥላሁንን ገድሎ አንገታቸውን ቆርጠው ወደመጡበት ሸሽተው አመለጡ፡፡

ወንድማማቾቹ የሸንቁጥ ልጆች በዕርግብዮት፤ በቅመጠት ገብርኤል፤ ጆማ ወንዝ፤ በጃማ፤ በሚዳ፤ በወረሞ፤ በታሞ፤በሸራፊት፤ በአመጸኛ ዋሻ፤ በሳድን፤ በደራ፤ በአደሬ፤ በሠባጌ፤ በወርቅ አምባና በሸማ ጅሩና በእንሳሮ ከጠላት ጦር ጋር በተለያዩ ግዚያት ተፋልመዋል፡፡

ልጅ አበበ ሸንቁጥ በተለያዩ ጦርነቶች በተደጋጋሚ ቆስለዋል፡፡

ግራዝማች ተሸመ ሸንቁጥ ጦራቸውን ይዘው አመጸኛ ዋሻ በመግባትና ከዚያ እየተንደረደሩ ጠላትን ለማጥቃት ቢያስቡም የጠላት




ልጅ አበበ ሸንንቁጥ ( በሁዋላ ደጃዝማች)ሕፃን ልጃቸውን ዓለማይሁ አበበን( በሁዋላ አምባሳደር) ዝናር አስነግተው በ1932 ዓ.ም. የተነሱት ፎቶ፡፡ ከጀርዳቸው ከቆሙት ከግራ ወደ ቀኝ መታፈሪያ ፤ካሣ ና ጠጋው ይገኙበታል፡፡



ልጅ አበበ ሸንቁጥ ልጃቸውን ሕፃን ዓለማየሁ አበበ ንዝናር አስነግተው
አጠገባቸው አድርገው በ1932 .ም. በመርሃቤቴ በረሃ የተነሱት ፎቶ

ሀይል በመጋቢት ወር መገባደጃ 1931 ዓ.ም.በዋሻው መግቢያ ላይ የመርዝ ጪስ በርሚሎች ሰቅሎ በማፈንዳት አርበኞችን ለእብደት ለዓይነ ስውርነትና በመጨረሻም ለሞት እየዳረጋቸወ ባለው ሁኔታ ግራዝማች ተሾመ ሸንቁጥ ተቀምጦ ሞትን ከመጠበቅ ተታኩሶ መሞትን በመምረጥ 267 ፈቃደኛ የሆኑ አርበኞችን አስከትለው ሌሊት ላይ እየተታኮሱ ከዋሻው አፋፍ እየተንከባለሉ ለቀው ሲወጡ በብዙ ቦታ ከመቁሰላቸውም በላይ የመርዙ ጪስ ዓይናቸውን ጋርዱዋቸው ነበር፡፡ ተከትለዋቸው የወጡት አብዛኞቹ ሲሞቱ የተረፉት ሰባት ብቻ ነበሩ፡፡ በሕይወት የሚገኙ ጥቂት አርበኞችን ይዘው በመሄድ ከልጅ አበበ ጦር ጋር ተቀላቀሉ፡፡ ግራዝማች ሕክምና ከተደረገላቸውና ካገገሙ በሁዋላ እንደገና ጦራቸውን አቁዋቁመው ትግሉን ቀጥለዋል፡፡

የሸንቁጥ ልጆች አምስት ሆነው "ዱሩ ቤቴ" ብለው በህይወታቸው ፈርደው አምስት አመት ያለእረፍት ጠላትን ካስጨነቁት መካካል ሦስቱ ለእናት አገራቸው ሕይወታቸውን መስዋዕት ያደረጉ ሰማዕታት ናቸው ፡፡ ሁለቱ በሕይወት ተርፈው የነጻነታችንን እድሳት በዓይናቸው ለማየት የበቁት ሰውነታቸው በጠላት ጥይት እነደወንፊት ተበሳስቶ ደማቸው የኢትዮጵያን ምድር ያቀለሙ ለጉድ የተረፉ ጀግኖች ናቸው፡፡



ወንድማማቾቹ ግራዝማቸ ተሾመ ሸንቁጥ( በሁዋላ ድጃዝማች) እና ልጅ አበበ ሸንቁጥ

(በሁዋላ  ደጃዝማች)  ስለቀጣዩ የጦርነት ስልት ሲመካከሩ የተነሱት ፎቶ 1932 ዓ፣ም.



ልጅ ኃይሌ ሸንቁጥ ( የእጅ ስዕል)

ሦስት ወንድሞቻቸውን በጦር ሜዳ፤ አመጸኛ ዋሻ ውስጥ ተጠልለው የነበሩትን ወይዘሮ ፋንታዬ የተባለቸውን አህታቸውን፤ አባትና እናታቸውን በመርዝ ጪስ አጥተው የተረፉት ግራዝማች ተሾመ ሸንቁጥና ልጅ አበበ ሸንቁጥ የደጃዝማችነት ማዕረግ ከቀዳማዊ ኃይለ ሥለሴተሰጥቶዋቸዋል፡፡

ከአምባሳደር ዓለማየሁ አበበ ሸንቁጥ

*የወንድማማቾቹ የሸንቁጥ ልጆች  የአርበኝነት ታሪክ ለአዲስ አበባ ዩኒቬርሲቴ ፕሬስ ለህትመት ቀርቡዋል፡፡